የሰ/መ/ቁ. 40305

ታህሣሥ 21 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ኢትዮጵያ ፐልፐና ወረቀት አ/ማ - ነ/ፈጅ አብዱልቃድር

**ተጠሪ፡-** እነ አቶ ታመነ ጫላ

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳዩ የጀመረው በአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪዎች ከሣሾች ሲሆኑ አመልካች ደግሞ ተከሣሽ ነበር፡፡

ተጠሪዎች በሥር ፍ/ቤት በተከሣሽ /አመልካች/ ላይ ባቀረቡት ክስ፤ አመልካች ተጠሪዎችን በጥበቃ የሥራ መደብ ቀጥሮ ሲያሰራቸው ቆይቶ ያለአግባብ ከሥራ ስላሰናበታቸው የሥራ መደባቸው በአ/ቁ. 377/96 አንቀጽ 10 መሠረት መሆኑ ቀርቶ በአንቀጽ 9 መሠረት ቋሚ ሠራተኛ አድርጎ ወደ ስራቸው እንዲመልሳቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ ጉዳዩን ለማየት ፍ/ቤቱ ስልጣን የለውም፣ የመክሰስ መብት የላቸውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቦ ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ተጠሪዎች የተቀጠሩት ሥራ ለማቃለል ለተወሰነ ጊዜ በመሆኑ ስራው ሲቃለል ማሠናበቱ አግባብ ነው፤ በመሆኑም ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪዎች በዚህ ውሣኔ ላይ ለምስ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ የወረዳ ፍ/ቤቱን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

በዚህ ውሣኔ ላይ ተጠሪዎች ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካች ተጠሪዎች የተቀጠሩት ሥራ ለማቃለል የተቀጠሩ መሆኑን ያላረጋገጠ በመሆኑ ተጠሪዎች ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሠራተኞች ናቸው በማለት አመልካች የአንድ ዓመት ውዝፍ ደመወዝ ከፍሏቸው ወደ ሥራቸው እንዲመልሣቸው በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታም ተጠሪዎች በአ/ቁ. 377/96 አንቀጽ 10/1/ሐ/ መሠረት የተቀጠሩ ሲሆን ስራው ሲቃለል መሠናበቻው አግባብ ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም የተጠሪዎች ስንብት ሕገ-ወጥ ነው የመባሉን አግባብነት ከተገቢው ሕግ ጋር በማገናዘብ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በማድረጉ ተጠሪዎች ቀርበው የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ተደምጧል፡፡

ከመዝገቡ እና ከክርክሩ ሂደት ተጠሪዎች ክስ የመሰረቱት በጥበቃ የሥራ መደብ ሲሰሩ ቆይተው በመሰናበታቸው የተቀጠሩበት ሥራ ቀጣይነት ያለው በመሆኑ ቋሚ ሠራተኛ ሆነው ወደ ሥራ እንዲመለሱ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ከዚህም የተጠሪዎች ክስ ተጠሪዎች ቀድሞውኑ የተቀጠሩት ለተወሰነ ሥራ ወይም ጊዜ መሆኑን ነገር ግን ሥራው ቀጣይነት ስላለው በቋሚነት ለመቀጠር የጠየቁ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ከአመልካች ክርክርና ማስረጃም ተጠሪዎች በአ/ቁ. 337/96 አንቀጽ 10/1/ሐ/ መሠረት መቀጠራቸውን ተገንዝበናል፡፡ በእርግጥ የአንድ የሥራ ውል በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 10 ሥር በተመለከቱት ሁኔታዎች የተደረገ መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር የሥራ ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ ይቆጠራል፤ የሥራ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ መደረጉን የማስረዳት ሸክም ያለበት ደግሞ አሠሪው ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎች የተቀጠሩት ለተወሰነ ጊዜ መሆኑን የፈረሙትን ውል በማቅረብ አስረድቷል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ የሰጠው ፍ/ቤት የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረገው የሥራ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ አልተደረገም በሚል ሣይሆን በእርግጥም አመልካች ተጠሪዎችን ሥራ ለማቃለል የቀጠራቸው ለመሆኑና ያሠናበታቸውም ሥራው በመቃለሉ መሆኑን አላስረዳም በማለት ነው፡፡ ነገር ግን ተጠሪዎች ለተወሰነ ጊዜ ሥራ ለማቃለል መቀጠራቸው ውሉ በሚገባ የሚያረጋግጥ ከመሆኑም በተጨማሪ ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ የሥራ ውላቸው በአዋጁ አንቀጽ 10 መሆኑ ቀርቶ በአንቀጽ 9 መሠረት ላልተወሰነ ጊዜ እንዲሆን መጠየቃቸው የተቀጠሩት አመልካች እንዳለው ሥራ ለማቃለል መሆኑን ያውቁ እንደነበርና በወቅቱ አመልካችና ተጠሪዎች የነበራቸው ሃሣብ ይኸው መሆኑን በሚገባ ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪዎች ሥራ ለማቃለል የተቀጠሩ ላለመሆኑ ያስረዱት ነገር የለም፡፡

ተጠሪዎች ሥራው ቀጣይነት አለው በማለት ያቀረቡትን ክርክር በተመለከተ ምንም እንኳን ስራው የአሠሪው ቋሚ ስራ ቢሆንም እንኳን መብዛት የሚኖርበት ጊዜ ሥራን ለማቃለል ለተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል መፈፀም የሚቻል መሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10/1/ሐ/ የሚፈቅድ በመሆኑ የተጠሪዎች ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች የተቀጠሩት ለተወሰነ ጊዜ በመሆኑ የአንድ ዓመት ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ሥራ ይመለሱ በማለት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 67773 በ14/11/2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የምስ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13061 በ05/02/2000 የሰጠውና የአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 16081 በ17/08/99 የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. ተጠሪዎች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 10/1/ሐ/ መሠረት ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ በመሆኑ ጊዜው ሲያልቅ መሠናበታቸው ሕጋዊ በመሆኑ ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ